😘የፒያሳዋ ወፍ

❤ምዕራፍ ❸

ስብሰባውን አጠቃልዬ የውሎ አበሌን ተቀብዬ ከግቢው ሳልወጣ ነው የደወልኩላት...ስልኳ ጥሪ አይቀበልም ይላል....አቤት አደነጋገጤ.. ምንድነው እንደዚህ ፍርስርሴ ያወጣው...?ነው አቅፌት ስጎመዣት ስላደራኩና እንዳልዋሀደት ስለተከለከልኩ ይሆን ...?መከልከሌ የፈጠረብኝ ወሲብ ረሀብ ይሆናል..መልሼ ሞከርኩ...አሁንም ደገምኩ...ይጠብቀኝ የነበረው ሹፌሬ ጋር ሄድኩና ገቢናውን ከፍቼ ገባው

<<ወዴት ላድርስህ ሀለቃ...?>>

<<አይ አንተን ላድርስህና መኪናዋን ፈልጋለው..አንድ ቦታ ምደርስበት ጉዳይ አለኝ...>>

<<እንደዛ ከሆነማ እኔ እዚሁ ልወረድና በተክሲ ልሂድ... እዚሁ ቅርብ ሳሪስ ነው የማድረው>>አለኝ... በወቅቱ ያለነው ላንቻ አካባቢ የሚገኘው የኦሮሚያ ፖሊስ ኮሚሽን ጽ/ቤት ውስጥ ነበር...

ይሉኝታም አላገደኝ<<እንደዛ ከሆነ ደስ ይለኛል>>አልኩት

እሺ ብሎ ቁልፉን እዛው እተንጠለጠለበት ትቶት ገቢናውን ለቆ በመውረድ<<..ነገ እንሄዳለን ወይስ እንውላለን>>

<<ነገ ቅዳሜ አይደለ .. ...?ካልቸኮልክ ብንውል ደስ ይለኛል>>

<<አረ እኔም ደስ ይለኛል>>

<<በል እሺ እንደዋወል>>አልኩትና ወደ ሹፌር መቀመጫ ቦታዬን ቀይሬ ቁልፉን አሽከርክሬ ሞተሩን አስነሳውና ግቢውን ለቅቄ በእስቴዲዬም አቅጣጫ ተፈተለኩ..የምሄደው ወደ ፒያሳ ነው..ሰዓቴን ተመለከትኩት 11፤15 ይላል በዚህ ሰዓት ፒያሳ ሄጄ ምን እንደማገኝ ለራሴም

አልገባኝም...የቤቷን አድራሻ አላውቅ...እሷ በዚህ ሰዓት ለስራ አትወጣ..እና ፒያሳ ደርሼ ምን ላደርግ ነው..ቸርቸር አካባቢ እንደደረስኩ ስልኬ ጮኸ..በቆሪጥ አየውት..አዎ እራሷ ነች እሷ ነች...በፍጥነት መኪናዬን የአስፖልቱን ጥግ ይዤ አቆምኩና አነሳውት

<<ሄሎ ሄሎ ..ሰላም ነሽ.....?እንዴት ነሽ....?አለሽ...?>> ተንሰፈሰፍኩ

<<አለው...ደህና ነህ..ሞክረህልኝ ነበር.....?ሰልኬ እኮ ቻርጅ ጨርሶ ነው>>

<<አይ ብዙም አልሞከርኩልሽም ...አንድ 20 ጊዜ ብቻ ነው...?>>

ሳቋን ለቀቀችው....ከወደ ገነት የተላከ መንፈስ አረጋጊ ጥኡመ ዜም መሰለኝ...

<<ትገርማለህ..እና የት ነህ...?>>

<<ወደ ፒያሳ እየመጣው ነው>>

<<ምን ልትሰራ...?>>

<<እንዴት... ....?ምን ልትሰሰራ ትያለሽ እንዴ...? ስልክሽ አልሰራ ሲለኝ ግራ ገብቶኝ ነዋ>>

<<እና ደረስክ አሁን>>

<<ቸርቸር አካባቢ ነኝ>>

<<እኔ እኮ ፒያሳ አይደለውም ...ሳር ቤት አካባቢ ነኝ>>

<<እና ልምጣና ልውሰድሻ>>

<<ታውቀዋለህ>>

<<አዎ ..>>

<<እሺ ከእስቴዲዬም ታክሲ ያዝና...>>ማብራሪያን ቀጠለች

<<መኪና ይዤለው>>አቋረጥኳት

<<መኪና አሪፍ ነዋ...ብስራተ ገብርኤል በቤተክርስቲያን አካባቢ ስትደርስ ደውልልኝ>>

<<ስልኬን ዘጋውና በእፎይታ እና በደስታ መኪናዬን አዙሬ በብሄራዊ አድርጌ በዋቤ ሸበሌ

ፊት ለፊት ወደ ሳር ቤት ነካውት

ያለችኝ ቦታ ደርሼ መኪናን ጥግ አስይዤ ካቆምኩ ብኃላ ...ደወልኩላት።...ከአስር ደቂቃ

በላይ አላስቆየችኝም...

ጉልበቷ አካባቢ የሚቀር ሮዝ አይነት ልዩ አይነት ቀሚስ ለብሳ... አንገቷ ላይ ሻርፕ ጣል

አድርጋ ...ባለረጅም ተረከዝ ጫማ ሰክታ..ከንፈሯን ሊፒስቲክ፤ አይኖቾን ኩል ተኩላ... ፀጉሯን

ግማሽ ተፈጥሮ ግማሽ ዊግ ደባልቃበትና ተሰርታው ጀርባዋ ላይ ዘፍ እንዲል አድርጋ ቀጭ

ቋ እያለች ወደአለውበት መጣች..አረ ይሄ ምኞቴ ነው..እሷን እየጠበቅኩ ባለውበት ቅፅበት

ያለምኩት...እንጂ እሷማ መች ስራ አጣችና...።

ነጭ እስኒከር ጫማ..ጉልበቱ የተባተራረፈ(ፍሽን መሆኑ መሰለኝ) ጅንስ ሱሪ...ጥቁር ሌዘር

ጅኬት እስከአንገቷ ቆልፋ ለብሳ እጆቾን ኪሷ ውስጥ ከታ እየነጠረች ፊቴ ገጭ ነው

ያለችው..ሊፒስቲክ የለ ቻፒስቲክ..ያ የተጠቀለለ ፀጉሯ እንኳን ወግ አልያዘም..ግን

እንዲያም ሆኖ የሆነ ልብን ቀጥ የሚያደርግ ውበት አላት..ማንም ሌላ ሴት ላይ አይቼው

የማላውቀው ውበት..>>ጉንጭ ለጉንጭ ከተሳሳምን ብኃላ በከፈትኩላት ገቢና ገባችና ከጎኔ

ተቀመጠች..

<<እሺ ወደ የት እንሂድ...?>>ጠየቅኳት

<<ወደፈለከው>>

<<ወደ ፈለከው ስትይ..ወደሀገሬም ቢሆን>>

<<ምንችግር አለው ...ያንተ ሀገር እኮ የእኔም ሀገር ነው..ሱዳን ወይ ኬኒያ ይዘኸኝ አትሄድ>>

<<የእወነት ግን ለምን ከከተማ አንወጣም>>

<<የት...>>

<<ደብረዘይት ወይም ናዝሬት...ጥዋት መልስሻለው>>

☎ +251-991192111 @stefantekka
+251-920-59-46-52 ✉ @achirlebwold አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ
E-Mail: stefantekka52@gmail.com Fax 251-11-11-11 Addis Ababa, Ethiopia

<<ንዳው>>ያልጠበቅኩትን ፈጣን ፍቃድ ነው ያገኘውት

<<ወዴት ልንዳው...?>>

<<ወደ አዳማ>>

<<ይመችሽ አልኩና በለቡ በኩል አድርጌ በአዲሱ መንገድ መኪናዬን ልክ እንደልቤ ሁሉ

በአይር ላይ እያንሰፈፍኩ ወደ አዳማ

<<መኪና ይዤለው ስትለኝ እኮ የራስህ መኪና መስሎኝ ገርሞኝ ነበር...>>

<<እንዴ !!!ለምን ይገርምሻል.....?

<<እኔ እንጃ እንዲሁ>>አለች እየተቅለሰለሰች..ምን ለማለት እንደፈለገች እንዲሁ

ተረድቼታለው

<<ያው የመንግስት ቢሆንም ቦታው ላይ እስካለው ድረስ የራሴው በየው>>

<<አይ እንዳዛ እኮ አይደለም ቦታው ላይ እስካለህ ድረስ ሳይሆን ..ያለህበት ቦታ የሚያዘውን

ስራ በምትሰራበት ጊዜ ብቻ ነበር ያንተ መሆን ያለበት..>>

<<አልገባኝም>>

<<እንዴት አይገባህም..አሁን እኮ አንድ ከስራው ጋር ምንም ግንኙነት የሌላትን ሴት

ጭነህበት ከስራው ጋር ምንም ግንኙነት ወደሌለው ቦታ እየሄድክ ነው...መንግስት ህዝብን

እንድታገለግልበት የሰጠህን መኪና ለግልህ ደስታ እየተጠቀምክበት ነው...እርግጠኛ ነኝ

ከዚህ አዳማ የምንሄድበትን ነዳጅ ከኪስህ ነው የሞላህው>>

<<ትቀልጂያለሽ...ለመኪናው መንግስት የሚመድብለት የራሱ ባጀት አለው እኮ..ለምንድነው

ከኪሰ የምቀዳው..የታዳሉት ሁለት ሶስት መኪኖችን በዚህም በዛያም ብለው የራሳቸው

ያደርጋሉ....አንቺ ወቅቶላ ከአዲስአባ አዳማ ለሚሄድበት ነዳጅ ቁምነገር ሆኖ እንዲሞላ

ትጠብቂያለሽ>>

‹‹አይ የታደሉት አልክ..እዚህ አገር ዘራፊ የበዛው ለምን እንደሆነ ታውቃለህ መዝረፍ

እንደእድል..እንደችሎታና ክብር ስለሚታይ ነው...እከሌ በሙስና እኮ ነው የተታሰረው ሲባል

ሰዉ አዕምሮ ውስጥ ሚፈጠረው ምስል...አንድ ሀብታም የተድቦለቦለ ፊት እና ያበጠ

ሰውነት ያለው...ብልጥ እና አምላክ የመረቀው...ብዙ የሚፈሩት እና ሚከያከብሩት ሰዎች

ያሉት..የታደለ ሰው አድርገን ነው...እንደእሱ ከመዋረድ አድነን ሳይሆን የእሱን እድል ለእኛም

አመቻችልን የዕድሜ ልክ መኖሪያችንን ቦጨቅ ቦጨቅ እናድርግና ብንታሰርም ሶስት አራት

አመት ነው...ለዛውም በድሎትና በምቾት.. ብለን ነው የምንጸልየው ››

‹‹አንቺ ፀረሙስና ውስጥ ነው እንዴ የምትሰሪው...?››

‹‹አይ አንተ.. ፀረ ሙስና እራሱ ሌላ ፀረ ሙስና ያስፈልገዋል››

‹‹ስንት አመቴ ነበር ያልሺኝ...?››

‹‹ቁጥሩን ከሆነ የፈለክ 19 ነኝ››

‹‹አይ ንግግርሽን ሳዳምጥ የ 29 መሰልሺኝ

‹‹ቀለድክ ማለት ነው.....?››

‹‹አልቀለድኩም ...ግን ጫወታ እንቀይርና በጣም ናፍቀሺን ነበር››

‹‹እንዲ በቃለሉ...ናፍቆት ማለት ትርጉሙ ጠፍቶሀል ማለት ነው..ዳሩ የዘመኑ ወንድ ልቡና

እንደበቱ አይተዋወቁም››

‹‹ማለት.....?››

ልባችሁ አስቦ እንኳን የማያወቀውን እንደበታችሁ ያንበለብለዋል.. አፈቀርኩሽ..ተከሰከስኩል

ሽ...ተፈጠፈጥኩልሽ በቃ ስትቀባጥሩ ትንሽ እንኳን አያደናቅፋችሁም››

‹‹አረ ተይ ጨፈጨፍሽን..ደግሞ ልባችሁ አስቦ ስትይ የሚታሰበው በልብ ነው እንዴ.....?››

‹‹እኔ እንጃ ..ፍቅር ግን በጭንቅላት የሚታሰብ አይመስለኝም..ስሜት ነክ የሆኑ ነገሮች

☎ +251-991192111 @stefantekka
+251-920-59-46-52 ✉ @achirlebwold አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ
E-Mail: stefantekka52@gmail.com Fax 251-11-11-11 Addis Ababa, Ethiopia

በልብ የሚቀመሩ ይመስለኛል..የሆነ ሰው ስታፈቅር ወዲያው ልብህ ምቱ ጨምሮ ድው ድው ሲል ታዳምጠዋለህ ...ጥሎህም ሲሄድ ህመሙ ቀድሞ ሚሰማህ ልብህ ላይ ነው..ልብህ ቀድማ ትደክማለች››

‹‹በፍቅር እና ጥላቻ ጥሩ ልምድ ያለሽ ይመስለኛል››

‹‹አይ በፍቅር ያለኝ ልምድ በጣም ኢምንት ነው..በጥላቻ ግን ዳቢሎስ እንኳን ሚበልጠኝ አይመስለኝም...››

‹‹መቼስ ካንጀትሽ አይደለም ..አንቺን የመሰለች የዋህ የፒሳ ወፍ..ከዳቢሎስ ጋር እንዴት እራሷን ታነጻፅራለች...?››

‹‹እወነቴን ነው..እግረ መንገዴንም እያስጠነቀቅኩህ ነው...ማለቴ እንዳትመሰጥብኝና አጉል እንዳትሆን ..››

‹‹ይህቺ ወደ ውስጥሽ እንዳልገባ በዙሪያሽ የገነባሻት አጥር መሆኗ ነው.....?ለማንኛውም ፖሊስ ነኝ..ፖሊስ በመሆኔ ደግሞ ፈተና ወዳለው...ታግዬ ማሸነፍ ተፋልሜ መርታት በቃ የሚመስጠኝ ተግባር ነው....››

‹‹እንግዲያው በህይወትህ የመጀመሪያው ወደሆነው ወደአስደናቂው እና አስቸጋሪ የፈተና ሜዳ እንኳን በሰላም ገባህ››

ፈገግ አልኩ..ምክንያቱም በዚህ ጮርቃ ዕድሜዋ በሴተኛ አዳሪነቷ እና ነበርኩ ባለችው የሌብነት ህይወት ውስጥ ያጋጠሞትን ጥቃቅን የህይወት ውጣ ውረዶች ባልበሰለው አዕምሮዋ አግዝፋና የአለምን ትልቁን ፈተናና መከራ ያሳለፈች አድርጋ አስባለች...አይ መከራ እቴ!! ከስንትና ስንት ወንጀለኛች ጋር ስባረር እና ስፋለም..ስንት ሙሰኞችን በተቀነባበረ እና በተወሳሰበ የምርመራ እና የክትትል ዘዴዬ ስጥል ያን ሁሉ ታሪኬን ብተሰማ እንዲህ እንደማንም የፒሳ አውደልዳይ ወጣት ቆጥራኝ አትንቀኝም ነበር››ስል አሰብኩ

መኪናዋን እያከነፍኩት ነው አዳማ እየተቃረብን ነው..ከክፍያው ጣቢያ አልፈን የከተማዋን ድንበር ተጠግተናል..የአባ ገዳ አካባቢ አልፈን ጥቂት ወደ ከተማዋ እንደገባን ድንገት

<<አቁም አቁም አለችኝ....>>

ደንግጬ ፍሬኔን ሲጢጢጥ አድርጌ አቆምኩ<<ምነው ምን ሆንሽ....?>>

አታያቸውም እነዛን ኮርመዎች..በቆምንበት የመንገድ ጠርዝ ወደውስጥ በሚያስገባ መንገድ ቅያስ ሁለት በሀያዎቹ ዕድሜ መጀመሪያ የሚገኙ ወጣት ወንዶች አንድ ታዳጊ ልጃገረድ በመሀከላቸው አድርጋው ከወዲህ ወዲያ ያንገላቷታል

<<መጣው ብላ ገቢናውን ከፍታ መውረድ ጀመረች>>

<<አረ እኔ እሻላለው ..አንቺንም ይተናኮሉሻል>>አልኮት ሽጉጤን ካስቀመጥኩበት አውጠቼ በጀርባዬ እየሻጥኩ....እኔ ከመውረዴ በፊት እሷ ስራቸው ደርሳ ነበር..አንደኛው ባለ በሌለ ኃይሏ ልጅቷ ላይ ጥፊ ሲሰነዝር የልጅቷ ፊት ላይ ከማረፉ በፊት ተምዘግዝጋ እጁን በአየር ላይ ቀለበችው..ፈጠን ብዬ ተጠጋዋቸው አንድ ሶስት ሜትር ሲቀረኝ ቆሜ መታዘብ ጀመርኩ ሆለ ደጀን መሆኔ ነው...

<<አንቺ ደግሞ ምን ሚሉሽ ነሽ....?>>

አሁን ሳትወረዱ በሰለም ልጅቷት ትታችሁ ጥፉ<<መሀል ያለችው ታጋች ልጅ በፍራቻና በድንጋጤ እየተንዘፈዘፈች እንባዋን ታነባለች>>

እጄን ወደ ወገቤ ልኬ ሽጉጡን ላውጣ እና ላስፈራራቸው ወይስ ትንሽ ልታገስ እያልኩ ነው

<<ነፍሱ ሰውዬሽን ተማምነሽ ከሆነ ይቅርሽ ..በማያገባሽ ጥልቅ እትበይ አላት>> ሌላው አይ ለእንደእናንተ አይነት ያልተቆነጠጡ ህጻናትማ እኔው በቃለው>>

ምን አንቺ ለእኛ..ደፋር ነሽ>>በድፍረቷ ተንከተከቱ..እውነቱን ለመናገር እኔም በንግግሯ ተገርሜያለው..ያው እነሱ እንዳሉተ በእኔው ተማምና ነው ስል ገመትኩና እራሴን ማዘጋጀት

ጀመርኩ...

ግን ወዲያው የሚስፈነጠር... የሚወናጨፍ ..የሚንሳፈፈ አካል ታየኝ..በሰከነዶች ሽርፍራፊ

ሁለቱም ጓረምሶች መሬት ተዘርረዋል..የእኔዋ ጂጄ እንደብሩስሊ እየተወነች ነው...ታጋቾ

ልጅቷ የበለጠ ደንግጣ መርበትበቷን ቀጥላበታለች..እኔም ከእሷ በላይ ደንግጫለው...

እንዴት እንዴት እርጋ ነው የዘረረቻቸው....?

ይህቺ ልጅ ወሬ ብቻ ሳተሆን እውነትም እንዳለችው መፈራት ያለባት አደገኛ ወፍ ሳትሆን

አትቀርም...ልቤ ፈራ

በአካባቢ ራቅ ራቅ ብለው ትዕይንቱን ሲከታተሉ የነበሩ ሰዎች በአድናቆት ያጨበጭቡላት

ጀመር ..ወዲያው ሁለት የአካባቢው ፖሊሶች ከየት መጡ ሳይባል ፊት ለፊቷ ገጭ አሉ

..እኔም ተንደርድሬ እናሱ ፊት ገጭ....እዳ ከሜዳ ይሏችሀል እንዲህ ነው...

..... ይቀጥላል

☎ +251-991192111 @stefantekka
+251-920-59-46-52 ✉ @achirlebwold አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ
E-Mail: stefantekka52@gmail.com Fax 251-11-11-11 Addis Ababa, Ethiopia